MIDROC Newsletter

Special Issue # 53

A BI-MONTHLY PUBLICATION OF THE OFFICE OF THE CHIEF EXECUTIVE OFFICER

This Newsletter provides customers, employees, suppliers, shareholders and the community at large with current information on major performance and other activities of the companies under the leadership of the CEO

Special Issue # 53 April 2017

# “ከታች ያለውን ሠራተኛ አሳውቀውም እያለክ ሥራን የምትሠራ ከሆነ ከላይ ተንሣፈህ ትቀራለህ” *

*በኢትዮጵያ አየር መንገድ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ለአሥር ዓመታት ያህል አገልግለዋል:: በአሜሪካ ታዋቂ ኩባንያዎች ውስጥ በምህንድስና ሞያ ለሃያ ዓመታት በመሥራት ውጤታማነታቸውን አስመስክረዋል:: በሥራ በቆዩባቸው ኩባንያዎች ባስመዘገቡት ስኬት ተደጋጋሚ ምሥጋና አግኝተዋል:: በሚሣይል መርሃ ግብሮችም ውስጥ ሞያቸው የሚጠይቀውን ሁሉ ያበረከቱ ሲሆን በተለይም በአሜሪካ የሮኬት አካላት ንድፍ ሥራ ውስጥ ተሳትፈው ያስመዘገቡት ውጤት ተጠቃሽ ነው:: በጥር 2003 ዓ.ም ተቀማጭነቱን አሜሪካን ሀገር ያደረገው Center for Creative Leadership (CCL) ለተመረጡ የሥራ ኃላፊዎች የሚሰጠውን ልዩ ሽልማት ከአፍሪካ የመጀመሪያው በመሆን አግኝተዋል:: ከ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ በኋላ አብሮ አደግ ጓደኛቸው ትውልደ ኢትዮጵያዊው ቢሊየነር ሼህ መሀመድ አሊ አላሙዲ ባደርጉላቸው ጥሪ ወደ አገራቸው መጥተው ሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕን በመምራት ላይ ናቸው:: የእርሳቸው የአመራር ተሞክሮ እነሆ!*



**የፒራሚዱ ጫፍ:-** ከወራት በፊት ከውጭ ሀገር ዩኒቨርሲቲ የተጨማሪ ሞያ ባለቤት የሚያደርግዎትን የዶክትሬት ዲግሪ አግኝተዋል:: ምን ሊሠሩበት አቀዱ?

**ዶ/ር አረጋ:-** ባለፉት ዓመታት የኼድኩባቸውን መንገዶች መለስ ብዬ ስቃኝ ሁለት አቅጣጫዎችን ይገፍ ተጉዣለሁ ማለት እችላለሁ:: በቀኝ በኩል ትምህርቱን በግራ ደግሞ ሞያን ጎን ለጎን ለማስኬድ ሞክሬያለሁ:: የምመራው ሥራ በባሕሪው ተለዋዋጭ /Dynamic/ ነው:: ዘመኑ ፈጣን ነው:: የተፈጥሮ ጉዳይ ነውና ዕድሜዬም እየጨመረ ነው:: ወጣት በነበርኩ ጊዜ ባገኘኹት ዲግሪና በሰበሰብኳቸው ልምዶች ብቻ ለሃያና ሠላሳ ዓመታት እየመራሁ’ና እየሠራሁ ልጓዝ ብል ውጤታማ መሆን አይቻለኝም::

ይኽን መነሻ አድርጌ በሥራ ያገኘኋቸውን ተሞክሮዎች በትምህርት ልደግፍ ስጥር ኖሬያለሁ:: የምማረው ዲግሪ ለመሰብሰብ ሳይሆን ትምህርቱ ለሥራው አስፈላጊ በመሆኑ ነው::

በምሕንድስና ሞያ በተመረቅሁበት የመጀመሪያ ዲግሪ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ አሥር ዓመት ያህል ሠርቻለሁ:: ቀጥሎም ስለ አየር ትራንስፖርት/Aviation/ ምሕንድስና ዕውቀት ሳይኖረኝ አየር መንገዱን ወደ ቀጣይ እርከን ለማሸጋገር በሚደረግ ጥረት የድርሻዬን ማበርከት ስለሚያዳግተኝ ተጨማሪ ዕውቀት ልገበይ ትምህርት ቤት ኼድኩ:: እናም እንግሊዝ ሀገር የአቪየሽን ትምህርት ተከታተልኩ::

ወደ አገሬ ተመልሼ ለትምህርት የተላክሁበትን ዓላማ ከግብ ማድረስ ጽኑ ፍላጎቴ ቢኾንም የወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ይኼን አልፈቀደልኝም:: ይሁን’ና አርፌ አልተቀመጥኩም:: በውጭ ሀገር በሞያዬ በተለያዩ ኩባንያዎች እየሠራሁ ኹኔታዎች እንድማር የግድ ሲሉኝ እየተማርኩ በርካታ ዓመታትን አሳለፍኩ:: ከጊዜ በኋላ ኩባንያዎችን የማስተዳደር ኃላፊነት መጣ::

ከመሐንዲስነት ወደ ኩባንያ መሪነት ሲመጣ መምራት ራሱን የቻለ ሣይንስ ነው’ና እንግዳ መኾን አይቀርም:: ስለዚህ ዘው ብዬ ኩባንዎችን ልምራ አላልኩም::

የመሪነት/Leadership/ ትምህርት ወደ ሚሰጥበት ተቋም ሔጄ መማር ጀመርኩ:: እናም በዚህ ዘርፍ ዶክትሬቴን አገኘሁ:: በኩባንያ መሪነት ንድፈ ሀሳብ ላይ መሠረታዊ ዕውቀት እንደጨበጥኩ ሲሰማኝ ወደ አገሬ በመምጣት የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ /CEO/ ኾኜ መምራት ጀመርኩ:: ባለፉት ዓመታት ኩባንያዎቹን በጥሩ መንፈስ ስመራ ቆይቻለሁ::

የቀድሞ የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ባለቤቶች ዩኒቨርሲቲውን ማስቀጠል የማይችሉበት ችግር በገጠማቸው ወቅት “…ይኼ ትልቅ ተቋም የሀገር ሀብት ነውና መውደቅ የለበትም:: ሲፈርስም ዝም ብሎ መመልከት ትክክል አይደለም::” የሚል ቁጭት የወለደው ሀሳብ በብዙዎች ውስጥ ይመላለስ ነበር:: ሼኽ መሀመድ እግዚአብሔር ይስጣቸውና መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ በግዥ ተረክበውት ተቋሙ እኔ ወደምመራው የሚድሮክ ቡድን (Group) መጣ::

ቀደም ሲል የምመራቸው ኩባንያዎች በትምህርት ላይ የሚሠሩ አይደሉም፤ ይልቁኑ ፋብሪካዎች’ና ኢንዱስትሪዎች ናቸው:: ወርቅ፣ እንቁላል፣ ስንዴ፣ ቆርቆሮ፣ ቀለም ወዘተ… ይመረትባቸዋል:: እነዚኽ ምርቶች ደግሞ ግዑዝ ናቸው:: በትምህርት ዓለም ደግሞ ምርት’ና አምራቾቹ ሰዎች ስለሆኑ ጥንቃቄው ለየት ማለት አለበት:: ምርቱ ተሸጦ ለጊዜያዊ ትርፍ የሚውል ሳይሆን ሀገርን የሚደግፍና የትውልድን ጉዞ የሚወስን ነው:: ስለዚኽ በትምህርት ሥራ ውስጥ አገልግሎት የመስጠቱና የመቀበሉ ጉዳይ የተማሪና የትምህርት ተቋሙ ብቻ አይሆንም::

የምትሰጠው ዕውቀት ለሀገር ቀጣይ ጉዞ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆን አለበት:: የትምህርት ተቋሙ መሪ ሆኜ ወደ ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ

---

★ *ዶ/ር አረጋ ይርዳው የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ቺፍ ኤግዚኪዩቲብ ኦፊሰር ያደረጉት ቃለ ምልልስ የፒራሚዱ ጫፍ ከተባለ መጽሐፍ ቅጽ 1፣ 2008 ዓ.ም. የመጀመሪያ ዕትም የተወሰደ*

ስኼድ ቁሳቁስ እንደ ማምረት "ይኼም'ኮ ቀላል ነው፤ ይቻላል። እንደ ሌላው ንግድ ይኼም በቃ ሥራ ነው።" ብዬ መኼድ በአስተሳሰብም ሆነ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ትክክል አልነበረም።

በመሆኑም ተቋሙን በስኬት እንድመራ በቅድሚያ እኔ መማር ይኖርብኛል ማለት ነው። ያደረግሁት ነገር ቢኖር የትምህርት አመራርና ለውጥ /Educational Leadership & Change/ የሚባል ኮርስ ወስጄ ስለ ትምህርቱ ዓለም አሠራር የተሻለ ግንዛቤ መፍጠር ነበር። ከሥርዓተ-ትምህርት /Curriculum/ ጀምሮ በትምህርት አስተዳደሩና አመራሩ ውስጥ ምን እንደሚሠራ ሳላውቅ በግብር ይውጣ ልምራው ብል ትክክል አይደለም። በእኔ ዕምነት ትምህርት ማብቂያ የለውም'ና መማር ጀመርኩ።

ይህ የዶክትሬት ትምህርት አራት ዓመት ወሰደ። እየተማርኩ ጎን ለጎን የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲን ተግባራዊ እንቅስቃሴ እየቃኘሁ የትምህርት አስተዳደሩን (Acadamics) አካባቢ ሳልጋፋ ተጓዝኩ። በቂ ዕውቀት ጨብጬ ከትምህርት አመራሩና ባለሞያው ጋር የጋራ ቋንቋ እስክፈጥር ድረስ በዚህ መልክ ቆየሁ።

የመመረቂያ ጽሁፍ የማዘጋጅበት ጊዜ ሲደርስ በአገራችን ከፍተኛ ትምህርት ላይ ትርጉም ያለው ጥናት ማድረግ እንዳለብኝ ተሰማኝ። ጥናቱን የዘመኑ ፈተና እየሆነ በመጣው የትምህርት ጥራት ላይ ማድረግ እንዳለብኝ ወስኜ ጀመርኩ።

በዚህ ላይ ማትኮሬ ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ጥራት ላይ የሚያደርገውን ትኩረት ከመረዳት፤ ቀጥሎም የግሉ ዘርፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማኅበር ፕሬዝዳንት እንደመሆኔ ጥናቱን በትምህርት ጥራት ላይ ባደርግ ሒደቱን በጥቂቱም ቢሆን 'ላግዝ እችላለሁ፤ ማኅበሩ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የሚሠራበት መድረክ ስላለው በሰብሳቢነቴ በተለይም በለውጥና ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ ላቀርብ እችላለሁ በሚል ነው።

ከዚህ በኋላም ሌላ ተጨማሪ ትምህርትን የሚሻ ኃላፊነት ቢመጣ እርሱን ለመምራት የሚያስችለኝን ዕውቀት ልሸምት ተማሪ ቤት እሔዳለሁ እንጂ ሽሽት አይሞከርም። በእኔ ዕምነት ራስን ከሚታየው እውነታ ጋር ካላስተካከሉ በስተቀር እመራዋለው የሚሉትን ጉዳይ አሳክቶ ከግብ መድረስ አይቻልም።

ስለዚህ የመሪነት ጉዞን ውጤታማ ሊያደርግ የሚችል አቅም መፍጠር የግድ ይላል። ያ አቅም ደግሞ ትምህርት ነው። ሰዎች በሕይወት ጉዞ ውስጥ ሁለት ነገር ይዘው መኼድ አለባቸው። የዛሬ ሠላሳ ዓመት የያዙትን ዲግሪ ግድግዳ ላይ ቢሰቅሉት ቀለሙ ወይቦ'ና ደብዝዞ ይገኛል። እንኳንስ ወረቀቱ ባለቤቱ እራሱ ይወይባል። በተከታታይ የመማሬ ዓላማ ይህ ነው።

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** ዩኒቲን ለመምራት የሚያስችልዎትን ትምህርት ከመውሰድዎ በፊት'ና አሁን ያሉበትን ሁኔታ በንጽጽር ሊገልጹልን ይችላሉ?

**ዶ/ር አረጋ፡-** ትምህርቴን በምከታተልበት ወቅት የመመረቂያ ጽሁፌን ያሳየኋቸው የትምህርት አስተዳደር አመራሮች በጽሁፌ በጎ ስሜት ሲያድርባቸውና ሲገረሙ ተመልክቻለሁ።

ትምህርቱን ከጨረስኩ በኋላ በየስብሰባውና በየጉባዔው ስለ ትምህርት ሣይንስ'ና ስለ ሥርዓተ-ትምህርት ሲነሳ የቀሰምኩት ዕውቀት ወቅታዊና ዘመኑ አሁን እየተገለገለበት ያለ በመሆኑ ከባለሞያዎችና ምሁራን ጋር ያለ ችግር መከራከርና መወያየት ችያለሁ።

የትምህርት ሣይንሱን በተመለከተ ብዙ ነገር አውቂያለሁ። ከምመራው የዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ ጋር በአንድ ቋንቋ መነጋገር መቻሌ ለኔ ትልቅ ስኬት ነው።

በጡረታዬ የመጨረሻው ጊዜያት ያካበትኳቸውን ትናንሽ ዕውቀቶች ክፍል ውስጥ ገብቼ ለወገን ለማካፈል አስባለሁ። ተገቢም ነው። ልምድህን ይዘህ መቃብር መውረድ የለብህም። ልምድ ለማካፈል ደግሞ እንደኔ እንደኔ ከዩኒቨርሲቲ የተሻለ ሥፍራ የለም። ምርኩዜን ይዤም ቢሆን ክፍል እየገባሁ ለተማሪዎች ካካበትኩት ልምድ ባካፍል ደስ ይለኛል። ለዚያ ደግሞ አሁን ያለሁበት ሁኔታ አመቺ ነው ብዬ አምናለሁ። በአጠቃላይ ትምህርቱን መውሰዴ ምቾት ሰጥቶኛል።

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** ከረጅም ዓመታት የባህር ማዶ ኑሮ በኋላ ወደሀገር ቤት ለመምጣት ምክንያት ስለሆኖት ነገር ጥቂት ያውጉን?

**ዶ/ር አረጋ፡-** እኔና ሼኽ መሀመድ በአንድ አካባቢ ለዚያውም ጎረቤት ኾነን ነው ያደግነው። የአንዳችን ወላጆች የሁላችንም ነበሩ ማለት ይቻላል። በኋላ ተለያይተን ለረጅም ዓመታት በየፊናችን እየባተልን ኖረናል። እርሳቸው ወደ ንግዱ ዓለም እኔ ደግሞ ወደ ትምህርቱና ተቀጥሮ ወደመሥራቱ ኼደን በየተሰማራንበት ስኬታማ ሆንን።

ከረጅም ዓመታት በኋላ ፈልገው አገኙኝና "አገሬን እየረዳሁ ነው። አሁን ሰው ያስፈልገኛል። አገራችንም ሰው ያስፈልጋታልና እርዳኝ" አሉኝ። በወቅቱ ይኼ ጥያቄ ለኔ ከባድ ፈተና ነበር። እድሜ ጠገብ ዳያስፖራ ነኝ። እንደ ሌሎቹ ትውልደ ኢትዮጵያውን አቻዎቼ ቁጭ ብዬ 'ወደ ኢትዮጵያ የማልሔደውማ ሁኔታዎች ስላልተመቻቹልኝ ነው' እያልኩ ሰበብ እየፈጠርኩ በጡረታ ዕድሜዬ አሜሪካ ትንሽ ዘና እንዳልል ይኽ ዓይነቱ ጥያቄ መጣ። አመጣጡ ደግሞ ከባድ ነበር።

አንደኛ ብዙ ሳይኖራት ተቸግራ ያስተማረችኝ ሀገር አለች። በሌላ በኩል ደግሞ አገሬን ልርዳ ያለ ወንድም እገዛ ያስፈልገኛል እያለ እንዴት እምቢ ማለት እችላለሁ? ልጆቼን ባሉበት ትቼ መምጣት ነበረብኝ።

ወደዚህ ስመጣ ሎስ አንጀለስ ውስጥ በሆሊውድ ቢቨርሊ ሆቴል የመጨረሻ ልጄን የትምህርት ምረቃ ሼህ መሀመድ ባደረጉት ልገሳ እያከበርን ነበር። ሼኽ መሀመድም በቦታው ተገኝተው ነበር። በል ቤተሰብ፣ ወዳጅ ጓደኞችህንም በዚሁ ተሰናበት!' አሉኝና በዝግጅቱ መድረክ ላይ የማልረሳውን ንግግር አደረጉ።

"…አረጋ ወንድሜና ጓደኛዬ ነው። ወደ ኢትዮጵያ ይገዤው ልኼድ ነው። እዚኽ ያላችሁ በሙሉ ፈቃደኞች ከኾናችሁ ትኬትና አስፈላጊውን ሁሉ ላቅርብላችሁ። ወደ አገራችን እንመለስ። ወደ አገራችሁ መኼድ ከፈለጋችሁ ሁሉን በማመቻቸት አሁኑኑ እንኳን ደህና መጣችሁ ልላችሁ እወዳለሁ።" የሚል ግብዣ አቀረቡ። በየቦታው ያሉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ እንዲመጡ ዕድል ሰጡ። ከነዚያ መካከል አንዱ ነኝ። ብዙዎችም የመጡ አሉ። ይኼው ዕድለኞች ነንና አገራችንን እያገለገልን ነው።

ለኢትዮጵያ ያላቸውን ፍቅር በአንደበቴ ዘርዝሬ ልገልጸው አልችልም። ስለ እውነት ከባድ ነው። አውሮፕላን ላይ ሆነው ቦሌን ቁልቁል በስስት እያዩ "ተመልከቱ እስቲ ሣሩን፣ እዩት እስቲ ልምላሜውን! ይኽችን'ኮ የመሰለ ምድር የለም!" ይላሉ።

በነገራችን ላይ የሼኽ መሀመድ ኢንቨስትመንት ለምን ጎልቶ አልወጣም? ይባል ይኾናል። እንደ ማንኛውም ባለ ሀብት በየቀኑ ሀብታቸው ባለበት ሥፍራ ሁሉ እየዞሩ 'ዛሬ ምን አተረፋችሁ? ያኛው የት ኼደ? ይኼስ ከየት መጣ?' የሚሉ ዓይነት ሰው ቢሆኑ ኖሮ ስለ ዕውነት የሀብታቸው መጠን ከአሁኑ እጥፍ በሆነ ነበር።

"ወንድሞቼ ናችሁ። ኃላፊነት ሰጥቻችኋለሁ። ኢትዮጵያ አገራችሁ ናት። የተሻለ አድርጉላት። ወገኖቻችሁን እርዱ። ከተቸገራችሁ ንገሩኝ።" የሚሉ ሰው ናቸው። በሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚነት ይኼው አሥራ አምስት ዓመት ቆይቻለሁ። አንድ ቀን "ማንን ቀጠርክ? ምን ዕቅድ አለህ? ምን ልታደርግ አሰብክ?" ብለው ጠይቀውኝ አያውቁም። ያቀድኩትን ስነግራቸው ቀጥል፣ በርታ ከማለት በስተቀር።

በነገራችን ላይ በሥራቸውና በባህሪያቸው ልዩ የሆኑ ሰዎቻችንን የማድነቅ ባህል ልንገነባ ይገባል። አትሌቶቻችንን እናደንቃቸዋለን። ምክንያቱም አስደናቂውን ነገር ለአገራችን ስለሚፈጽሙ! ይኼ ትክክለኛና ተገቢ ነው።

የሊቢያ ፕሬዚዳንት የነበሩት ሙአማር ጋዳፊ የአፍሪካ ኅብረት ዋና ጽህፈት ቤት ወደ ትሪፖሊ እንዲኼድ ቅስቀሳ ባደረጉበት ወቅት የኢትዮጵያ ጉድለት ነው ብለው ካራገቧቸው ነጥቦች መካከል ዋናው

የመሠረተ ልማት ችግር በተለይም ለመሪዎችና ዲፕሎማቶች የትራንስፖርት አቅርቦት አለመኖሩ ነበር፡፡ ይኼን ተከትሎ በሁለት ሳምንት ውስጥ ስድሳ ማርቼዲስ መኪናዎችን በአውሮፕላን አንጉዘን አመጣን፡፡ መኪኖቹን ሀገሪቱ እንግዶችን እንድታስተናግድበት ዕርዳታ ሰጡ፡፡

በሚሊኒየም ዋዜማ ዲያስፖራው በስፋት እንደሚመጣ ስለ ታመነ ዝግጅት ተጀመረ፡፡ ለክብረ በዓልና ለስብሰባ የሚሆን ሃያ ሺህ ሰው የሚይዝ አዳራሽ አስፈለገ፡፡ ስድስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ብረት'ና ሚስማር ጭምር ከውጭ በአውሮፕላን ተጭኖ መጥቶ ሚሊኒየም አዳራሽ ተገነባ፡፡ ማነው ካለ አንዳች ትርፍና ጥቅም ይኽን የሚያደርግ? ከኢትዮጵያ በስተቀር አንድ ያገሬው ባለ ሀብት ይኼን ሁሉ ያደረገበት ሀገር የት ነው?

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** መልካም ስራ የሰሩ ሰዎችን የማወደስ ባህላችን በእጅጉ አነስተኛ ነው ብለው ነበር፡፡ "ነብይ በሀገሩ አይከበርም!" የሚለውን ዕድሜ ጠገብ ብሂልም በተደጋጋሚ ጊዜ ይጠቀማሉ፡፡

**ዶ/ር አረጋ፡-** ከጥንት ጀምሮ በአገሯ የበቀለ 'ነቢይ' ከማይከበርባት ሀገር አንድዋ ኢትዮጵያ ትመስለኛለች፡፡ ሌሎች አገሮች 'ነቢዮቻቸውን' ያከብራሉ፡፡ ከመካከላቸው ጠቢብ ቢፈጠር፤ አንስታይን ቢከሰት… አገራቸውን ከፍ አድርገው ለማሳየት ይጠቀሙበታል፡፡ እኛ ዘንድ ግን ነገሮች በተቃራኒው ናቸው፡፡

የባህል ችግር አለብን ብዬ አስባለሁ፡፡ ሰውን በሥራውና ባለው መልካም ነገር ማወደስና ማመስገኑ ላይ እስከዚህም ነን፡፡ ይኽ ባህል ከየት መጣ? እውነቱን ለመናገር አላውቅም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከመግባባት ላይ መድረስ ያለብን ይመስለኛል፡፡ አንድ ቀላል ምሳሌ ልስጥ፡፡

አንተ ለፍተህ ጥረህ ግረህ የሰውን ዓይን የምታማልል አንዲት መኪና ስታሽከረክር ብትገኝ በእግሩ የሚኼደው አብላጫው ስለአንተ በመደሰት ፈንታ በክፉ አይን እያየህ እንድትሸማቀቅ ያደርግሃል፡፡

ግን ለምን? በእኔ ዕምነት ያቺ መኪና ኢትዮጵያ ውስጥ ከገባችበት ሰዓት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሀብት ናት፡፡ ትናንት መገለጫችን ሌላ ነበር፡፡ 'ወገኔ ይህችን የመሰለች ወርቅ መሣይ መኪና እየነዳ ነው፡፡ ያድርግለት! እኔም ከሠራሁ ነገ ተስፋ አለኝ፡፡' ብሎ ሁኔታን በቀና መልኩ ለማየት የሚሞክረው ጥቂት ነው፡፡

'አኻ! ይኼን ሰውኮ ትናንት አውቀው ነበር፡፡ ይኼን ሀብት ያገኘው ሠርቆ መሆን አለበት፡፡' ቶሎ ብለን የምንኼድበት አቅጣጫ አሉታዊ ነው፡፡ ይኼ ባህል መሰበር ይኖርበታል፡፡ ብዙ ሰው የሚሞገሰው የቀብሩ ዕለት ነው፡፡ በብዙ ቀብሮች ላይ ተገኝቻለሁ፡፡ በአንዱም ሥፍራ ሃቅ ሲነገር አልሰማሁም፡፡ "ሟች እዚህ ቦታ ታስሮ፣ እዚህ እዚህ ቦታ ይኼን አድርጎ ነበር፡፡" ብሎ እውነቱን መናገር ለእኛ ዳገት ነው፡፡

ሰው ከሞተ ወዲያ ቀና ቀናውን መናገር እንጂ ሙትን መውቀስ ምን ያደርጋል? ከሞተ ወዲያ ለምን በክፉ እናነሳዋለን?' በማለት ብንዋሽ በጉዳዩ ትክክል አለመሆን ተስማምተን በአደባባይ ሙት ወቃሽ ላለመሆን ማሰባችን መልካም ነው፡፡

ጥሩ የሠራ ሊሞገስ የሚገባው እስከሆነና መልካም ተግባራት እስካሉት ድረስ በሕይወት ያለውን ሰው ማሞገስ ደግሞ አወንታዊና ጠቃሚ ነው፡፡

ለሚሞገሰው ሰው ለቀጣይ ሥራውና ማንነቱም የሞራል ስንቅና ጉልበት ኾኖት የተሻለውን ለዓለም ሊያበረክት ይችላል፡፡ ምናልባትም በሰሰትንበት ሙገሳ መጠን ለተስፋ መቁረጥ ዳርገነው ጉዳት ልናደርስበት እንችላለን፡፡

ፈረንጅ ትንሽ ሲደረግለት 'አመሠግናለሁ!' ይላል፡፡ የእኛ ሀገር አንዳንዱ ሰው ራርተህ አንዳች ነገር ብትሰጠው 'ይኽችን ነው እንዴ የሚሰጠኝ?' ይልሃል፡፡ ሼኽ መሀመድ በየጊዜው ከሚደርስባቸውና ከሚያስደንቁኝ ነገሮች አንዱ ይኽ ነው፡፡ ቸር ናቸውና ድንገት ተነስተው ለሰዎች ገንዘብም ኾነ ሌላ ስጦታ ደስ እንዳያሰኛቸው ይሰጣሉ፡፡ 'እንዴ ይኽችን ብቻ ነው እንዴ የምትሰጠኝ?' የሚሏቸውም አሉ፡፡ እግዚአብሔር ያሳያችሁ! የሰው'ኮ ገንዘብ ነው፡፡ መቅደም የሚገባው ምሥጋና አልነበረምን?

ሼኽ መሀመድ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ሰዎች ያደረጓቸው መልካም አስተዋጽኦዎች ዕውቅና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ታሪክ እኮ ነው፡፡ አንዳንዴ የዛሬ መቶና ሁለት መቶ ዓመት የነበረን አንድ መንግሥት በጭፍን ጥሩ ነበር እንላለን፡፡ ያንኑ በመልካም ያነሳነውን መንግሥት ድንገት ተነስተን መቶ በመቶ ስህተት ነበር እንላለን፡፡ መቼም ሰው ፍፁም አይደለምና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሰራውን ክፉና ደግ መግለጽ ሁሉም ሰው ሊያስብበትና ሊተገብረው ይገባል፡፡

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** የአንድ ስኬታማ መሪ መገለጫው ምንድነው?

**ዶ/ር አረጋ፡-** ስኬታማ መሪ በሰው ላይ አተኩሮ የሚሠራ ነው፡፡ ሥራህን የሚሠራው'ኮ ከታች ያለው ባለሞያ ነው፡፡ የብዙ ሥራ መሪዎች ችግር ሰው ላይ አለማተኮር ነው፡፡ ሠራተኛን በሁለት መንገድ ብትመለከቱት መልካም ነው፡፡ አንደኛ ሰው በመሆኑ በስብዕናው ሁለተኛ ደግሞ በሚሠራው ሥራ፡፡ ሁለቱን ለይታችሁ ማየት አለባችሁ፡፡

ድንገት ሠራተኛችሁ ቢያጠፋ ጥፋቱ በሥራው አጋጣሚ የተፈጠረ እንጂ ከሰውየው አመጣጥ፣ ታሪክ'ና ማንነት ጋር የተያያዘ እንደኾነ አድርጋችሁ የምታስቡ ከሆነ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ ሥራውን እንዲያስተካክል ልትረዱት ይገባል፡፡

ኑሮውን፣ የግል አኗኗሩንና ስብዕናውን እየጠቀሳችሁ ሠነፍ ነው እያላችሁ መውቀስ ኢ-ሚዛናዊነት ነው፡፡ ከተጨባጩ እውነታ ያራርቃችኋል፡፡ እነዚኽን ለያይቶ መመልከት የሚችል ጥሩ መሪ ነው፡፡ ጥፋት አጠፋ ተብሎ ሰራተኛን ለማጥቃት መነሣት ከጥሩ መሪ የሚመነጭ አይደለም፡፡ ሰውዬውን እንደ ሰው መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በሰው ላይ ካላተኮሩ በስተቀር የሚኬድበት መንገድ ጠቃሚ አይሆንም፡፡ በኩባንያ ውስጥ እነዚኽን ነገሮች መለየት የሚችሉ ሰዎች ስኬታማ መሪዎች ናቸው፡፡

በአመራር እርከን ወደ ከፍታው በወጡ'ና አለቃ እየሆኑ በኼዱ ቁጥር ፒራሚዱ ጫፍ ላይ መድረስ ይመጣል፡፡ ያኔ ከሥር ያሉትን ሠራተኞች መዘንጋት አይገባም፡፡ ሰዎች ወደ መጨረሻው የኃላፊነት ጫፍ ይወጣሉ፡፡ ፒራሚዱ መሠረት የለሽ ከሆነ ከፒራሚዱ አናት ላይ ያሉ ሰዎችም አይኖሩም፡፡ ስለዚህ ከታች ያለውን ሠራተኛ መርሳት አይገባም፡፡

መሪዎች ፒራሚዱን ከታች ወደ ላይ ከላይ ወደ ታች እየተንቀሳቀሱ መሠረቱ አለመናጋቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እንዲህ ያለ የመውጣትና የመውረድ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ስኬታማ መሪዎች ናቸው፡፡ ፒራሚዱ ጫፍ ላይ ነው ያለሁት ከታች ያለውን አላውቀውም እያሉ የሚመሩ ሰዎች አየር ላይ ተንጠልጥለው ይቀራሉ፡፡

**የፒራሚዱ ጭፍ፡-** የሀገር ውስጥ የበረራ አድማሳችሁን አስፍታችኋል፡፡ በአየር ትራንስፖርት ዘርፍም አዲስ አቅጣጫ የያዛችሁ ይመስላል፡፡ ኩባንያዎቻችሁም በቁጥርና በመጠን እየጨመሩ ናቸው፡፡ እንደ መሪ የቀየሱት የማስፋፊያ ስትራቴጂ ነው?

**ዶ/ር አረጋ፡-** ቁም ነገሩ ኩባንያዎቹ በቁጥር መብዛታቸው አይደለም፡፡ የሀገርን ሕግ ከማክበር አኳያ በጥበብ ለመራመድ ስለፈለግንም ነው፡፡ ሁለት ምሳሌዎችን ላንሳ፡፡ ሆም ዴፖ የተባለው ኩባንያችን ከውጭ ሀገር ዕቃ አስገብቶ 'ራሱ ይቸረችር ነበር፡፡

መንግሥት ያወጣው አዲስ ሕግ ደግሞ "አንድ አስመጪ ኩባንያ ዕቃ ማስገባት'ና በጅምላ ማከፋፈል መብቱ ነው፡፡ ነገር ግን መቸርቸር አይፈቀድለትም" ይላል፡፡ ካስገባ ያከፋፍላል እንጂ አይቸረችርም፤ የሚቸረችር ከሆነ ደግሞ አስመጪ መኾን አይችልም፡፡ ይኽን ሕግ ተቀብለን ከመንግሥት ጋር አብረን መጓዝ አለብን፡፡

ሕጉን ተቀብለን መፍትሔ ይሆናል ያልነውን ዘዴ መመሪያ'ና ደንቡን ባከበረ መልኩ ተገበርን፡፡ ነገሩ ቀላል ነበር፡፡ ሆም ዴፖ ውስጥ አስመጪ የነበረውን አንድ የሥራ ክፍል ነጥለን በማውጣት አስመጪ ኩባንያ አቋቁመን ፈቃድ አወጣን፡፡ ሌላኛው በችርቻሮ ሥራ ራሱን ችሎ ቀጠለ፡፡

ኩባንያዎቻችን ቁጥራቸው የሚያድገው በዚህ መልኩ ህግን ለማክበር በምናደርገው ጥረት ነው።

ኮስፒ እና ኤም.ቢ.አይ ኩባንያዎቻችን የሚያመርቷቸውን ምርቶች በየቦታው ለወኪል ቸርቻሪዎች ብቻ በመስጠት ፈንታ እኛም እነዚኽን ምርቶች ለሕዝብ እናቅርብ ካልን ሆም ዴፖ ኩባንያን አቋቁመን የችርቻሮ ሥራ መተግበር ግድ ይላል። ይኽ አካኼድ ሌላም ጥቅም አለው። ኩባንያዎቹ ተጣምረው እርስ በርስ እየተባበሩ እንዲጓዙ ያደርጋል።

ሁለተኛውን ምሳሌ ልስጥ። ሃያ አንደኛ ሆኖ የመጣው ሚድሮክ ጂኦ ኤክስፕሎሬሽን ሰርቪስ ማዕድን አዲሱ ኩባንያችን ነው። በለገደንቢ የተጀመረው የወርቅ ምርት ሥራ ወደ ሣካሮም ተሻገረ'ና ተስፋፋ።

በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መተከል ላይ ለአሥር ዓመት ያህል አሰሳ አድርገናል። ኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥትም ሆነ የግል ድርጅቶች የሌሏቸው ምርጥ የኤክስፕሎሬሽን መሣሪያዎች አሉን። የሚሰረስሩ፣ በስርሰራው የተገኙትን ፍንጮች የሚተነትኑ ዘመናዊ ላቦራቶሪዎች'ና በማዕድን ፍለጋ በእጅጉ የተካኑ ባለሞያዎችም አሉን።

በሥራው የተወሰነ የወርቅ ክምችት አግኝተናል። ከግኝቱ በኋላ ያለው ቀሪ ሥራ እያመረቱ ለዓለም ገበያ ማቅረብ ነው። ከዚህ በኋላ አሰሳ የሚያደርጉ፣ ፍንጮችን የሚተነትኑ ወዘተ… ባለሞያዎቻችን፣ መሣሪያዎቻችን'ና ላቦራቶሪዎቻችን ሥራ ሊፈቱ አይገባም የሚል ውሳኔ ላይ ደረስን።

እነዚኽን ምርጥ ባለሞያዎች'ና ዘመናዊ መሣሪያዎች በከንቱ ማስቀመጥ ብዙ ሥራ መሥራትና ውጤት ማስመዝገብ ሲችሉ እጃቸውን እንደ ማሠር ነው። ስለዚኽ አንድ ነገር አሰብን።

አገልግሎታችን ለሀገር ነው። ይኽን ቡድን ይዘን ከነመሣሪያው የጂኦሎጂ፣ የቁፋሮ ወይም የስርሰራ'ና የላቦራቶሪ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ራሱን የቻለ ኩባንያ አቋቋምን። ኩባንያው ሚድሮክ ወርቅን እንደ አንድ ቋሚ ደንበኛው ይይዛል።

ሚድሮክ ወርቅ ኩባንያውን ሥራ ማሠራት ሲፈልግ ገንዘብ ከፍሎት ኮንትራት ገብቶ አገልግሎት ማግኘት ይችላል። በሌላ አንጻር ማዕድን የመፈለግ'ና የማውጣት ሥራ መሥራት እየቻሉ በመሣሪያና ባለሞያ እጦት ምክንያት የተቀመጡ ከሚድሮክ ውጭ የሆኑ በርካታ ድርጅቶችና አካላት አሉ። ይኽ ኩባንያ ለእነዚኽ'ና ለሌሎችም አገልግሎት ይሰጣል።

Trans National Airways (TNA)ን ውሰደው። እኔ አርባ ዓመት ሙሉ በበረራ ቴክኖሎጂ (Aviation) ውስጥ አልፌያለሁ። የቀድሞ ታሪኬ በአብዛኛው ኤሮ ስፔስ (Aerospace) ነው።

የዛሬ አሥራ አምስት ዓመት እዚኽ ስመጣ ዳሽ ኤይት የሚባሉ ሁለት ትናንሽ አውሮፕላኖች እያንዳንዳቸው በአሥራ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ተገዝተው ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ተቀምጠው ነበር።

ሼኽ መሀመድ አውሮፕላኖቹን ያስመጧቸው ሥራቸውን ለማስፋፋት'ና ለመንቀሳቀስ ነበር። እግዚአብሔር ጸጋውን አበዛላቸው'ና እነዚኽን ትተው ትላልቅ'ና የተሻሉ ዘመናዊ አውሮፕላኖች ገዙ። ሁለቱ (Dash-8) አውሮፕላኖች ቦሌ ላይ ብዙ ጊዜ ሳይሠሩ እንደተቀመጡ አወቅን።

እኔ በመጣሁ ጊዜ ሚድሮክ ኢትዮጵያ አንዳንዴ ለድንገተኛ ሥራ ጂቡቲ ይልካቸዋል። በተረፈ ሥራ ስለማይኖር ቦሌ ላይ ይቀመጣሉ። የራሳቸው ፓይለቶችና የጥገና ባለሞያዎች አሏቸው። ለዚኽ ሥራ ሲባል የተከራዩት ቢሮ አለ። ሠሩ አልሠሩ ደሞዝ ይከፈላቸዋል። መለዋወጫው የሚገዛው ከውጭ ሀገር ሲሆን ገንዘቡን የሚያወጡት ሼኽ መሀመድ ናቸው።

ይሄ ትልቅ ኪሳራ ነበር። እነዚኽ ጠቃሚ አውሮፕላኖች ያለ ሥራ ተቀምጠው ምን እያደረጉ ነው? አልን። አውሮፕላኖቹን'ና አብራሪዎቹን ይዘን በቀጥታ አዲስ አየር መንገድ አቋቋምን።

በዚኽ እንቅስቃሴ ውስጥ እያለን እንደ ልብ እንዳንሠራ ሕግ አገደን።

አዋጁ የሀገር ውስጥ የግል አየር መንገድ ኩባንያ የሚፈቀድለት የመንገደኛ ብዛት ሃያ ብቻ ነው ይላል። በንጉሡ ጊዜ የወጣ አዋጅ ነው።

አምሳ መንገደኞችን ማጓጓዝ እንዲቻል'ና መንግሥት ሕጉን እንዲያሻሽል ለማድረግ አሥራ ሁለት ዓመት ፈጅቶብናል። አሁን በቅርቡ ተፈቅዶ ተግባራዊ ኾኗል።

ሃያ መንገደኞችን ብቻ ማጓጓዝ በሚፈቀድበትም ጊዜ ቢሆን እንቅፋት ገጠመን ብለን አርፈን አልተቀመጥንም። ለሃያ መንገደኞች ብቻ የሚበቃ መቀመጫ ትተን ቀሪዎቹን ከአውሮፕላኑ ውስጥ አውጥተን ልንሠራ ሞከርን።

ፈጽሞ አዋጭ አልሆነም። መቀመጫዎቹን ወደነበሩበት መልሰን ሊቢያና ሱዳን አምሳ'ና ከዚያ በላይ መንገደኞችን ማጓጓዝ ወደ'ሚፈቀድባቸው አገሮች ልከን አከራየናቸው። እንዳቀድነውም ራሳቸውን ችለውልናል።

በአገራችን ሕጉ ተሻሽሎ አምሳ መንገደኞችን የሚያጓጉዝ አውሮፕላን ሲፈቀድ ከያሉበት አመጣናቸው።

ኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥት ሆኖ የኖረው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ብቻውን በቂ አይደለም የሚል ዕምነትም ነበረን። ሌሎች አየር መንገዶች መፈጠር አለባቸው። ጤናማ ውድድር'ና ለበለጠ ሥራ የሚያነሳሳ ተግዳሮት (Chalenge) መፈጠር አለበት። በሌላውም ሀገር የሚደረገው ይኼው ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግዙፍ ኩባንያ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ግዙፍ እየኾነ በኼደ መጠን በግሉ ዘርፍ የተሰማሩትን አየር መንገዶች በሥሩ በአክሲዮን መልኩ እያደራጃቸውም ቢኾን የሀገር ውስጡን በረራ ለቀቅ አድርጎ ሊያሳድጋቸው ይገባል።

አንድና ብቸኛ ኩባንያ ሆኖ የሚቀጥል ከኾነ ምናልባትም ውድድር ካለመኖሩ የተነሳ የአቪየሽን እድገትና ክህሎት ከማጠናከር አኳያ አሳሳቢ ያደርገዋል። በዚኽ መንፈስ ተግባብተን መደበኛ (Scheduled Flight) እንዲፈቀድልን አድርገናል።

ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ውጭ ስኬጁል ፍላይት ተፈቅዶልን እየበረርን ነው። በዚያ መልኩ ነው TNA የመጣው።

እርሱ ብቻ አይደለም የንግድ ሔሊኮፕተር ገዝተናል። በአገራችን የሔሊኮፕተር በረራ ሕግ እንዲኖር የተቻለንን እያደረግን ነው። እንደእኛ በዕድገት ላይ ያለና በየቦታው የእርሻ፣ የማዕድን፣ የኮንስትራክሽን…ወዘተ ስራዎችን እያስፋፋ ያለ ሀገር የሔሊኮፕተር አገልግሎት ያስፈልገዋል።

የታመሙ ሰዎችን በፍጥነት ለማጓጓዝ፣ አደጋ የደረሰባቸውን ለመታደግ፤ የአየር ላይ ካርታ ለማዘጋጀት…ወዘተ የሔሊኮፕተር ድጋፍ ያስፈልጋል። ስለዚኽ የሔሊኮፕተር አገልግሎት በአገራችን እንዲኖርና እንዲስፋፋ ራዕይ ስለነበረን ጀምረናል።

በሌላው ሀገር ሔሊኮፕተር ትልቅ ሥራ እየሠራ ነው። እኔ እኮ ከዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ በመኪና ተነስቼ እዚህ እስክደርስ አንድ ሰዓት እየፈጀብኝ ነው። ግን እኮ ዩኒቲ ላይ የሔሊኮፕተር ማረፊያ ቢኖረኝ በፍጥነት ከዚኽ ወደዚያ ከዚያ ወደዚኽ መመላለስ እችላለሁ።

ቅንጦት አይደለም ጉዳዩ ሥራ ነው። ይህን መሰል አሠራር የማይቀርና ወቅቱን ጠብቆ የሚመጣ እውነታ ነው። በሌላው ዓለም እኮ በልዩ ልዩ ሕንጻዎችና በሆስፒታሎች ላይ ማረፊያዎች ተሠርተው ሰዎች በሔሊኮፕተር ወዲኽና ወዲያ ይላሉ። የሂደት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ይኽ ለአገራችንም የማይቀር ነው። በመከልከልም ሊቆም አይችልም።

ይልቁኑ አገልግሎቱ ለደኅንነት ስጋት እንዳይሆን ሥርዓት መዘርጋት እንጂ በመከላከል መግታት ልክ አይደለም።

እንግዲህ ሂደቱን ጀምረነዋል፤ ሕጉን አክብረን እናደርገዋለን። አስፈላጊውን የህግ ማዕቀፍና ድጋፍም እያገኘን ነው። በእርግጥ ሔሊኮፕተር እንደ አውሮፕላን አይደለም። መንግሥት ተባብሮን

ሕግና ሥርዓትን አጠንክሮ ማበረታታት ይጠበቅበታል፡፡

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** በኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ታሪክ ውስጥ የኩባንያ አመራርን ከአባት ወደ ልጅ በውርስ ማሻገር የተለመደ ነው፡፡ አስተዳደሩን ለባለሞያ መስጠት የሚደፈር አይደለም፡፡ የኩባንያን አመራር ለባለሞያ መስጠት ጥቅሙ ምንድን ነው?

**ዶ/ር አረጋ፡-** አንድ ባለ ሀብት ኩባንያ አቋቁሞ ራሱ ሲመራው ቆይቶ ወደ ልጆቹ ማስተላለፉ በአገራችን የተመለደ'ና የመጣንበትም አካኼድ ነው፡፡ ጉዳዩ ልጆችን ለሥራው ብቁ አድርጎ ከማዘጋጀት ጋር የተያየዘ ነው፡፡ ልጆቹ ዕውቀትና ልምዱ ካላቸው የባለሀብቱ ልጆች በመ'ኾናቸው ብቻ መገለል አይኖርባቸውም፡፡ እንዲያውም ለአውራሹ መልካም አጋጣሚ ነው፡፡ ችግሩ ወላጆች ጥሩ ኩባንያ ካቋቋሙ በኋላ በስተእርጅ'ና የደረሰ ልጅ ካለ በዕውቀት'ና በክህሎት ሳይዘጋጅ ልጅ ስለሆነ ብቻ ድንገት ኩባንያውንም አመራሩንም የማውረስ ነገር ሲሆን ነው፡፡

ልብ አድርጉ ልጁ እንደ ወላጆቹ የለፋበት ድርጅት ላይሆን ይችላል፡፡ ድንገት እጁ ላይ ጠብ ያለ ንብረት ነው፡፡ የራዕዩም አካል ላይሆን ስለሚችል ሊያበላሸው ይችላል፡፡

በአብዛኛው ስኬታማ ነበሩ የሚባሉ ወላጆች ኩባንያዎቻቸውን ለልጆቻቸው ካወረሱ በኋላ ሥራው እንደ ወላጆቹ ዘመን ትርፋማነቱን ይዞ ሲቀጥል አይስተዋልም፡፡

በውርስ ከማስኬድ በተጨማሪ በኩባንያ አመራር ክህሎቱና ዕውቀቱ ያላቸውን ሥራ አስፈፃሚዎች በመቅጠር ሥራውን ውጤታማ ማድረግ ጥሩ አማራጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዓለማችን ታላላቅ ኩባንያዎች ባለቤቶች መካከል አንዱ የሆነው የማይክሮሶፍት ባለቤት የቢልጌት የሕይወት ተሞክሮ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይኾናል፡፡

ቢልጌት በትምህርቱ ብዙ አልገፋም፡፡ ነገር ግን ሠርቶ ሀብታም ሆኗል፡፡ ቢሊየነር ነኝ ብሎ አርፎ አልተቀመጠም፡፡ ሥራ አስፈፃሚ ፍለጋ ነው የኼደው፡፡ ሲፈልግ አንድ ሰው አገኘ፡፡ ያም ሰው አብሮት የተማረ'ና እርሱ ትምህርቱን ሲያቋርጥ እስከ ዶክተሬት ዲግሪ ድረስ የቀጠለ ጓደኛው ነው፡፡ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አድርጎ ሾመው፡፡ በቤተሰብ አሊያም በዘመድ ሊያስመራ ይችል ነበር፤ ይኼን ግን አላደረገም፡፡

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** ኩባንያችሁ እየሰፋ ቁጥሩም እየጨመረ በኼደ መጠን የአስተዳደር መዋቅሩ ምን ይመስላል?

**ዶ/ር አረጋ፡-** በሌላው ዓለም በተለይ በምዕራቡ ሆልዲንግ ካምፓኒ (Holding Company) በሚል አሠራር ኩባንያዎችን አጣምሮ መሥራት የሚያስችል ሕግ አለ፡፡ ይኸ ማለት አንድ ኩባንያ ሌሎች ኩባንያዎችን እየገዛ ከራሱ ጋር እያደባለቀ እያንዳንዳቸው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አደረጃጀት ኖሯቸው ገቢያቸው'ና ወጪያቸው አንድ ላይ የሚተዳደርበት አሠራር ነው፡፡

ሆልዲንግ ካምፓኒ በአገራችን ገና ሕጉ አጥጋቢ በሆነ መልኩ አልወጣም፡፡ የጊዜና የሂደት ጉዳይ ነው፡፡ ጊዜው ደርሶ ነገሮች በዚያ መንገድ መታየት እስኪጀምሩ በሕጉ መሠረት የሚያመቸንንና በሕግ በማያስጠይቅ መልኩ የኩባንያ አስተዳደር ዘይቤ ተከትለን እየሠራን ነው፡፡

የሆልዲንግ ካምፓኒ ጠቀሜታ ሠራተኞችን በአንድ ላይ አድርጎ ከሥፍራ ሥፍራ የሚለያየውን የመሪዎች ብቃት እየመዘኑ ባለሞያዎችን ከዚኸ ወደዚያ ከዚያ ወደዚኸ እያዘዋወሩ ኩባንያዎች እንዲተጋገዙ የማድረጊያ'ና ጥምረት የመፍጠሪያ አሠራር ነው፡፡

ስለዚኸ እያንዳንዳቸው ሕጉን አክብረው የሚሠሩ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ናቸው፡፡ ነገር ግን ሊተባበሩ የሚችሉበትን አንድ ሥርዓት መዘርጋት ይቻላል፡፡ ለዚህም ብለን ቢሮ ከፈትን፡፡ ያ! ነው እንግዲህ የዋና ሥራ አስፈጻሚ ቢሮ የሚባለው፡፡

ይኼ የዋና ሥራ አስፈጻሚ ቢሮ ለኹሉም የሚድሮክ ኩባንያዎች የአስተዳደር'ና የአመራር አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ እንዲዋቀር አድርገናል፡፡ ምክንያቱም ሕጋዊ መሆን ነበረበት፡፡ ስለዚህ ከሃያ አንዱ ኩባንያዎች አንዱ ሚድሮክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚባል የማስተዳደርና የመምራት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ተቋቋመ፡፡ ሌሎቹ ሃያዎቹ ከዚህ ቢሮ ጋር የአመራር አገልግሎት ለማግኘት ኮንትራት ገብተዋል፡፡

ይኽ የዋና ሥራ አስፈጻሚ ቢሮ ለሚሰጣቸው የአመራር'ና የአስተዳደር አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፡፡ እያንዳንዱ ኩባንያ በዋና ኃላፊዎች ስለሚመራ ይኽን ሥርዓት ከዘረጋሁ በኋላ የኹሉንም ኩባንያዎች ተግባር መመልከት አያስፈልገኝም፡፡ በቀድሞው አሠራራችን ግን ኹሉንም ዋና ሥራ አስኪያጆች የማየው እኔው ነበርኩ፡፡

አሁን ግን ሚድሮክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ቢሮ የሚለውን ሥርዓት ከዘረጋሁ በኋላ አራቱን ኩባንዎች ለአንድ ተቆጣጣሪ ኃላፊ (Principal Operation Officer) የሚል ፈጥረን እነዚሁ ኃላፊዎች በሥራቸው ያሉትን ድርጅቶች በበላይነት እንዲከታተሉ አድርገናል፡፡ እነዚኽ ደግሞ በሥራቸው ዋና ሥራ አስኪያጆች አሏቸው፡፡

ወደ እኔ ልምጣ'ና ካሉት ሃያ አንድ ኩባንያዎች መካከል ቢያንስ አንዱን በሙሉ ኃላፊነት የማልመራ ከኾነ የዋና ሥራ አስኪያጅነትን ሥራ አላውቀውም ማለት ነው፡፡ ዋና ሥራ አስኪያጆች የሚያጋጥማቸውን ችግር'ና የሥራ ኹኔታው የሚፈጥረውን ጣጣ ልገነዘብ አልችልም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ውስጥ ግዙፍ የኾነውን ሚድሮክ ወርቅ ማዕድንን በዋና ሥራ አስኪያጅነት እየመራሁ ነው፡፡

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት ዩኒቲ ዩኒቨርስቲን ለመምራት አነሰም በዛም መማር'ና ሌላ ሌላም ነገር ስላስፈለገው በእኔ የአመራር ጥላ ሥር እንዲኾን አድርጌያለሁ፡፡ ወርቅ ማዕድኑ የኢንጂነሪንግ ዕውቀት ስለሚያስፈልገው'ና በሞያዬም ለሥራው ቅርብ ስለሆንኩ በእኔ ይመራል፡፡

በዋናነት በእኔ ሥር ላሉ ኩባንያዎች ማንኛውም ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚሠራውን ስራ እሠራለሁ፡፡ ከዚያ የምማረው ቁም ነገር ለሌሎችም እንዲደረስ ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ሌላው እንግዲህ የቡድን ምክክርና የስራ አፈፃፀም ምዘና ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡

እኛ ዘንድ ሠራተኛው ብቻ ሳይሆን እያንዳንዳቸው ኩባንያዎች በቡድኑ ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ይደረግባቸዋል፡፡ ያንን ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት የሃያ አንዱም ኩባንያዎች ዋና ሥራ አስኪያጆች ቁጭ ብለው ይፈትሻሉ፡፡ መመሪያው አንድ ዓይነት ስለሆነ ሁሉም ይማማሩበታል፡፡ በተመሳሳይ ዕውቀት'ና አቅም ተጋግዘው እንዲጓዙ አደርጋለሁ፡፡

አስፈላጊ ሲኾን ደግሞ ኃላፊዎቹን እናዟዙራቸዋለን፡፡ በአንዱ ኩባንያ ውስጥ ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበረው ሰው ሌላ ኩባንያ ዘንድ ኼዶ እንዲመራ ይደረጋል፡፡ አንዱ የሌላውን የሥራ ባህሪ'ና የአመራር ሥርዓት ሲረዳ ሚድሮክን የበለጠ ያውቃል፡፡

በአንድ የሚድሮክ ኩባንያ ለምሳሌ በፋይናንስ ባለሞያነት'ና ኃላፊነት ሲሠራ የቆየ ሰው ከፍ ወዳ'ለ ኩባንያ ተዛውሮ እንዲመራ እናደርገዋለን፡፡ ዕድል ሰጠነው ማለት ነው፡፡ ይኽንን ዝውውር ስናደርግ እንዲሁ በግብር ይውጣ ሳይኾን ሕጋዊ አግባብና ሞያዊ አካኼድ ጠብቀን ነው፡፡

አንድ ኃላፊ ከአንድ ኩባንያ ወደ ሌላ በሚዘዋወርበት ወቅት የአገሪቱ ሕግ በሚያዘው መሠረት የመብት ጥበቃ ተደርጎለት ነው፡፡

የአመለካከት ችግር ከሌለብን በስተቀር አንድን ኩባንያ ሲመራ የቆየ ሰው ሌላ ኩባንያ ላይ ሲመደብ ለመምራት የሚቸገርበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ ሥራውን ምራ፤ ሠራተኛውን ፍሬያማ መኾን በሚችልበት ዘዴ አስተዳድር ተባለ እንጂ ምርቱን አንተ አምርት አልተባለም፡፡

ወርቅ ማዕድንን ምራ እንጂ ወርቁን ወይም ድንጋዩን ቆፍር አልተባለም፡፡ መሪነት ችሎታ ነው፡፡ የመሪነት ብቃት አለኝ ብሎ ሲመራ የኖረ ሰው ሌላው ቀርቶ መንፈሳዊ ተቋምን እንዲመራ ቢላክ ሊመራ ይችላል፡፡ እኔ ሎስ አንጀለስ ውስጥ የአንድ ቤተ- ክርስቲያን ሊቀመንበር ኾኜ በደንብ መርቻለሁ፡፡

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** ከዚህ ቀደም ባደረጓቸው ቃለ ምልልሶች በቢዝነስ ዓለም ሕግን አክብሮ በመሥራት ላይ አትኩረው ብዙ ተናግረዋል። በተለይ ወጣት የቢዝነስ ሰዎች ዘላቂ'ና ስኬታማ እንዲሆኑ በሥነ ምግባር ላይ ክፍተት መፍጠር የለባቸውም ሲሉም ይደመጣል። ስጋትዎ ከምን የመነጨ ነው?

**ዶ/ር አረጋ፡-** ለራሱ አደላ ካልተባልኩ በስተቀር የእኛ የወጣትነት ዘመን ማለትም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች የነበርንበት ጊዜ ወርቃማ ሊባል የሚችል ነበር። በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ያሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጭምር በአንድ ላይ የለውጥ መንፈስ እንዲያንሰራራ መሠረት የጣሉበት ዘመን ነበር።

1960 እ.ኤ.አ. በአገራችን መሬት ለአራሹም ሆነ ሌላ ሌላውም እንቅስቃሴ የተፈጠረበት ነው። በዚያን ጊዜ የነበረው ወጣት'ና የአሁኑ አንድ አይደሉም።

አንድ ዓይነትም ራዕይ የላቸውም፤ ምንአልባትም ሊኖራቸው ግድ አይልም። ያ ጊዜ ማለት ብሔራዊ ስሜት የገነነበት ነበር። በእርግጥ ያ! ስሜት አሁን ጭራሹኑ ጠፍቷል ማለት አልችልም።

በእኛ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ማለት በሚያስችል መልኩ ትኩረታችን ብሔራዊ ስሜት ላይ ነበር። ቀስ እያለ የዓለማችን ሕዝብ በአብላጫው ዓለም አቀፋዊ ሆነ'ና ከዚኽ ቁጭ ተብሎ ዋሽንግተን፣ ኒውዮርክና በሌላውም ዓለም እየተከናወነ ያለውን ድርጊት በእፍታው ወደምናውቅበት የቴክኖሎጂ ዘመን ላይ ደረስን። ዓለም ትንሽ መንደር ኾነች ተባለ። ገንዘብ ዋነኛው ገዥ ሆኖ አረፈ።

"…ሀብት ካለኽ የሆነ ትርጉም ያለው ሰው ነኽ፤ ከሌለህ ደግሞ የለህም።" የሚለው የጋራ ዜማ መሆን ጀመረ። በአንዳንዱ የዓለማችን ክፍል መማር ትልቅ ክብር'ና ቦታ አለው።

በአንዳንዱ ዘንድ ደግሞ ከትምህርት ይልቅ ሀብት የበለጠ ክብር አለው። እኔ ለሃያ ዓመታት በኖርኩበት ምዕራቡ ዓለም የሰው ሚዛን "…ምን ተማረ ሳይሆን ምን አለው?" የሚለው ነው። ወደ ኋላ ሔደን የእኛን ሀገር የቆየ ባህል ብናስታውስ "ምን ተምሯል?" በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ነበር። ቀስ በቀስ ያ ስሜት'ና ዕምነት እየወረደ ቁሳዊ ሀብት የበላይ እየሆነ የመጣበትን እውነት እያየን ነው። በአሁኑ ጊዜ በየከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱ እየተማረ ያለው አብዛኛው ወጣት ዕውቀቱን ቢጨብጥም ባይጨብጥም በኾነ መንገድ ተመርቆ ስለመውጣት የሚያልም፤ ዕውቀቱ ኖረም ቀረም የተሰጠችኝን ፈተና ብቻ ልለፋት'ና ሌላው የራሱ ጉዳይ የሚል አስተሳሰብ የያዘ መኾን ለዚህች ሀገር አሳሳቢ ነው የሚል ዕምነት አለኝ።

አንድ ተማሪ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመርቆ ሲወጣ ሌላው ቢቀር መጠነኛ የሆነ ለሥራ የሚሆን ዕውቀት ሊኖረው ይገባል። ፈተናውን ለማለፍ ብቻ የተማረ መሆን የለበትም። ፈተናውን በተፈተነ ቁጥር ትንሽ ትንሽ ዕውቀት አጠራቅሞ መውጣት ነው ዓላማው እንጂ የተፈተንከውን ሁልጊዜ ታስታውሳለህ ማለት አይደለም። ሳታውቀው አብሮ የሚዘልቅ ዕውቀት ይዘህ ትወጣለህ ለማለት ነው።

አሁን አሳሳቢ የሆነው አብዛኛው ሰው ትምህርትንና ዕውቀትን የማንነቱ መለኪያ በማድረግ ፈንታ የምማረው ትምህርት ገንዘብ እስካመጣልኝ ድረስ ሌላው ትርፍ ነው በሚል አስተሳሰብ እየተገዛ መምጣቱ ነው። ይኼ ዓይነቱ ወጣት ትኩረቱና ሩጫው ገንዘብ የሚያገኝበትን መንገድ ማሰስ ብቻ ይሆን'ና ሕጋዊና ሕገ ወጡን መንገድ እንዳሻው እየቀላቀለ ሊዋኝ ነው።

ይኼ ያስፈራል። በአቋራጭ መክበር ማለት "…ገንዘብ ላግኝ እንጂ ገንዘቡ የሚገኝበት ሒደት እንዳሻው ቢኾን አይገ'ደኝም" እንደ ማለት ነው። "…ሲሻኝ ልስረቅ፣ ልቅጠፍ፣ አየር በአየር ልነግድ፣… ላወናብድ፣የፈለገው ይሁን ብቻ የሆነ ሀብት ላግኝ።" የሚል ነው። ይኼ ጉዳት አለው። አብላጫው የአዲሱ ዘመን ወጣት ባለሀብት በዚያ አስተሳሰብ ውስጥ መምጣቱ ራሱን እንደ ስኬታማ ሰው እንዲቆጥር ያደርገዋል።

የተደጋገመ ውሸት የእውነት ያኽል ይቆጠራልና ትውልዱም ይኼን "ስኬት" ለመኮረጅ ሲራኮት ይታያል። በአቋራጭ መንገድ ኺያጁም እንደ ጀግና'ና እንደተሳካለት ሰው ተቆጥሯልና ቀጣይ ሕይወቱም ያው በመጣበት ሕገ ወጥነት የተቃኘ ይሆናል። ስለዚህ ራሱን ብቻ ሳይሆን ሀገርን ሁሉ እያበላሸ ይቀጥላል።

በአቋራጭ ወደ ሀብቱ ሠገነት ለመድረስ የምንጠቀምበት ሒደት ያሰብነውን ያመጣልን ይሆናል። ነገር ግን ሀብት'ና ሥልጣን ያለ ዕውቀት አደገኞች ናቸው።

በዚያ በተሳሳተ መንገድ ኃብታም የኾነ ሰው በማኅበረሰብም ሆነ በግለሰብ ደረጃ በእጅጉ አስፈላጊ የሆነውን የቤተሰብ ሕይወት እንኳን መምራት ሲቸግረው ይታያል። ልጁን የሚያስተምረው ከሀብቱ አኳያ እየመዘነ ነው።

ብዙ ገንዘብ ስላለው ልጁን ከፍ ያለ ዋጋ ወደሚጠይቅ ትምህርት ቤት ይልካል። ለእርሱ ምርጡ የትምህርት ሥፍራ ያ ነዋ! እዚያ ከፍተኛ ገንዘብ አውጥቶ በሚያስተምርበት ሥፍራ በሚሰጠው ትምህርት ልጁ ነገ ምን ዓይነት ሰው እንደሚሆን እንኳን መገመት አይፈልግም።

እየተፍጨረጨረም ቢኾን ትክክለኛውን መንገድ የያዘ ባለሀብት ያገኛት እሴት የብዙ ድካም ውጤት መኾኗን አሳምሮ ያውቃል። የድካሙን ውጤት ወደ ቀጣይ እርከን ለማሸጋገር መክፈል ያለበትን ዋጋና የሚጠብቀውንም ድካም ያውቃል። ስለዚህ ኹሌም ይማራል። ብዙም ርቀት ይጓዛል።

በአንድ ጊዜ ሀገር ጉድ ያሰኘ ሚሊየነር ላይሆን ይችላል። ነገር ግን ሕይወቱ በየዕለቱ በእርካታ የተሞላች ትኾናለች። ኀበዝ! ሕይወት በገንዘብ ብቻ የምትተመን ከኾነ ዋጋዋ ዝቅ እያለ ይኼዳል። ስለዚህ ደስታችንን በገንዘብ ብቻ መለካት የለብንም።

"…የፈለገው ይኹን። አጭበርብሬ፣ ለዚህም ለዚያም ጉቦ ሰጥቼ፣ አቅምሼ… ብቻ ቶሎ ልክበር" የሚሉ ሰዎች ልክ እንደ አበባ ናቸው። አበባን ከቆረጥከው በኋላ ለአራትና አምስት ቀን ያህል ያምራል። ሲሸትም መዓዛው ልዩ ነው። ግን ቶሎ ይከስማል። ይወድማል። ምክንያቱም ከምንጩ ተቆርጧል። ከዋናውና ከትክክለኛው ሥፍራ ሊመጣ የሚችለው ውሀና ምግብ፤ ሊያሳድገው የሚችለው ንጥረ ነገር ተቋርጧል። ተፈጥሯዊ ዕድገቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ከተፈለገ ሳይቆረጥ የሚፈልገውን ውሀ እያጠጡ'ና እየተንከባከቡ ውበቱ ቀጣይ እንዲሆን ማድረግ ነው። በዚህ መንገድ ከተያዘ እየፋፋ፣ እያፈራ'ና እየተስፋፋ ይኼዳል።

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** በመሪነት ጉዳይ ላይ ሲናገሩ በጣም ተመስጠው ነው። በእርግጥ የኩባንያዎች መሪ ስለሆኑ ብቻ ነው ወይስ ሌላም ነገር አለ?

**ዶ/ር አረጋ፡-** ባገኘሁት አጋጣሚ በመሪነት (Leadership) ላይ ተመስጬ የምናገረውና በዚያ ላይ የማተኩረው በአገራችን የአመራር ክፍተት አለ ብዬ ስለማምን ነው።

የኩባንያ መሪዎች ባለ ራዕይ ከሆኑ ድርጅቱን እንዴት ነው የማሳድገው? የዛሬ አምሥት ዓመት… አሥር ዓመት ኩባንያዬ የት መድረስ አለበት? ወደ'ሚለው ጊዜ ተሻጋሪ አስተሳሰብ እንዲመጡ እፈልጋለሁ። ዛሬ ተኮር ብቻ ከሆኑ በጥቃቅን የአስተዳደር ሥራዎች ይዋጣሉ። በራዕይ የሚመሩ መሪዎች ብዙ አይደሉም፤ እንዲበዙ ግን ምኞቴ ነው።

በአስተዳዳሪና በመሪ መካከል ያለው ልዩነት የታወቀ ነው። አስተዳደር ሥራው ማስተዳደር ነው። በዕለት ተዕለት ሥራ ላይ ያተኩራል። የሚፈረም ነገር ካለ ይፈርማል። በጀት ወጥቷል፤ በበጀቱ መሠረት ነገሮች እየተጓዙ መሆናቸውን ይቆጣጠራል። መሪ እርሱን መሥራት የለበትም። ወጣ ብሎ አዲስ መንገድ የሚቀይስበትን መቆስቆሻ ይዞ መመለስ አለበት።

መሪ ማተኮር ያለበት ስንት ተወዳዳሪ ኩባንያዎች መጥተዋል? የሚኼዱት ወዴት ነው? የአንድ ተወዳዳሪ ኩባንያ በሀገር ውስጥ መፈጠር ለእኔ ይዞት የሚመጣው በጎ ነገር ምንድነው? ደንበኞዬ ምን እየፈለገ ነው? በሚሉት ነጥቦች ላይ ነው ።

የአገራችን ባለሣር ክዳን ቤቶች በአብዛኛው በቆርቆሮ ተለውጠዋል፡፡ ቀጣዩ የሰው የለውጥ ፍላጎት በምን ላይ ያተኩራል? ዓለም አቀፉ የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ እየተለወጠ ነውና የኩባንያዬን ስትራቴጂ በምን መልኩ ልቀይር?...ወዘተ የሚሉና ሃያ አራት ሰዓት አፍንጫቸው፣ ጆሯቸው'ና ዓይናቸው የሰላ ንቁ'ና ለምርምር ትኩረት የሚሰጡ መሪዎች በብዛት መፈጠር አለባቸው፡፡

በየዘርፉ የአመራር እጥረት አለብን፡፡ በፖለቲካው፣ በንግዱ፣ በሀይማኖቱ፣ በወታደራዊው... በየትኛውም ሞያ የመሪነት እጥረት አለብን፡፡

የአመራር ዕውቀት በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ በዚኽ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ በሁለተኛ ዲግሪ የአመራር ጥበብን (Leadership) በተመለከተ ትምህርት መስጠት ጀምሯል፡፡ ይህም ከላይ የጠቀስኩትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በሥሬ ባሉት ኩባንያዎች በአብዛኛው በመሪነት ላይ ያሉ ይኽንን የአመራር ሥርዓት (Leadership) ትምህርት እየተከታተሉ ነው፡፡ በዚኹ አጋጣሚ ይኽ ዕድል ለሕዝቡም ክፍት መኾኑን ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** በሕይወትዎ ረክተዋል? ደስተኛስ ነዎት?

**ዶ/ር አረጋ፡-** እንዴታ! እርካታ መጠን አለው ከተባለ እኔ ከመጠን በላይ ረክቻለሁ፡፡ የሕይወቴ ጉዞ ነገውኑ ቢቋረጥ እንኳን እኔ በጣሙን የረካሁና የተሳካልኝ ሰው ነኝ ብዬ አምናለሁ፡፡ ተልዕኮዬን በአግባቡ አሳክቻለሁ፡፡

ያሉብኝን የቤተሰብ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች ተወጥቻለሁ፡፡ ዘጠኝ ልጆችና አሥር የልጅ ልጆች አይቻለሁ፡፡ ሁሉም የተማሩ ናቸው፡፡ የእያንዳንዱ ሰው የመጀመሪያው ትልቅ ኃላፊነት ቤተሰብ ነው፡፡ ሀገር የሚሆነው የቤተሰብ ጥርቅም ነው፡፡ ቤተሰቡን በአግባቡ መርቶ ወደ ስኬት ያላመጣ መሪ ነኝ ቢለኝ አይገባኝም፡፡

ይኽች ሀገር ያስተማረችኝ እየከፈለችኝ ነው፡፡ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርሲቲውን ትምህርት እንኳ ብትቆጥር ወደ አሥራ አራት ዓመት በነጻ ተምሬያለሁ፡፡ እንግዲህ ይኼ ዕዳ ነበረብኝ፡፡ ዕዳዬን በተገቢው ሁኔታ እየተወጣሁ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ለእያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ቆይታዬ የሁለት ዓመት አገልግሎት ብሰጥ እንኳን እዳዬን በመጠኑም ቢሆን እንደከፈልኩ እቆጥራለሁ፡፡

እኔ የተማርኩት አሁን በማስተዳድራቸው ኩባንያዎች ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ወላጆች በወቅቱ በከፈሉት ግብር ነው፡፡ የነዚያ ግብር እየከፈሉ ያስተማሩኝን ወገኖች ልጆች "አለቆቼና ጌቶቼ!" እያልኩ ከልቤ አክብሬ እያገለገልኳቸው ነው፡፡ይኼ ያረካኛል፡፡

በሌላ አንጻር አንድ ሰው ከታገለ ካሰበበት ሊደርስ እንደሚችል በንድፈ ሃሳብ ሳይሆን በተጨባጭ ያረጋገጥኩ በመሆኔ በእርግጥም የረካሁ ሰው ነኝ፡፡ አለቃዬም እንዲሁ ለፍተው'ና ጥረው በርካታ መሰናክሎችን አልፈው እንዲህ ካለው አስደናቂ ሥፍራ መድረሳቸው፤ እኔም ፊደል ቆጥሬ አሁን እናንተ "ለተምሳሌትነት እንፈልግኻለን!" እንዳላችሁኝ በዚኽ መንገድ የሚጠቀስ ሰው መኾን በመቻሌ ደስተኛ ነኝ፡፡

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** የሼኽ መሀመድ አላሙዲ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት በአገሪቱ አጠቃላይ ጉዞ ውስጥ ያለው ሥፍራ የቱ ጋ ነው ይላሉ?

**ዶ/ር አረጋ፡-** ይኽንን ለመመለስ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ "አገሪቱ ከዛሬ ሃያ ዓመት በፊት ምን መልክ ነበራት?" የሚል ጥያቄ ማንሳት ይኖርብናል፡፡

ሼኽ መሀመድ የውጭ ባለ ሀብት ፈጽሞ ፊቱን ወደ ኢትዮጵያ ስለማዞር በማያስብበትና አገሪቱ በሮችዋን ከፍታ ባለሀብቶችን ባልጠራችበት ወቅት "አገሬና ወገኖቼ ዘንድ ኼጄ አለማለሁ፡፡" ብለው ስጋቶችን ሁሉ አሽቀንጥረው ጥለው ሀብታቸውን ይዘው የመጡ የአዎንታዊ ሀሳብ ባለቤት ናቸው፡፡

ልብ አድርጉ! እርሳቸው ለኢንቨስትመንት በመጡበት ወቅት አገሪቱ ከኤርትራ ጋር ውጊያ ላይ ነበረች፡፡ ጦርነት አለ ብለው አልሸሹም፡፡ እንደ ባለሀብት ይኼን ጨርሶ ጥያቄ ውስጥ አላስገቡም፡፡

ሼኽ መሀመድ "አንዳንድ የተማሩ የአገሬ ሰዎች ቢኖሩ ሔጄ ላስተባብራቸው፡፡ እነርሱ በዕውቀታቸው እኔ ደግሞ በገንዘቤ ይኽችን ሀገር እናልማ፡፡" ያሉ የቁርጥ ቀን ልጅ ናቸው፡፡ "በጤናው እገሌን፤ በእርሻው እገሌን፤...ልያዝና እስቲ ልጀምር..." ብለው ልባቸውንና ፊታቸውን ወደ አገራቸው ማዞራቸው የተለዩ ሰው ያደርጋቸዋል፡፡

ኢንቨስትመንት በተፈጥሮው ሥጉና ፈሪ ነው ይባላል፡፡ ባለ ሀብት ለኢንቨስትመንት ሲነሳ የት ሔጄ ነው ገንዘቤን የማዳብረው? እዚያ ሀገር ሔጄ ሙዋለ ነዋዬን ባፈስ ምን ያህል አተርፋለሁ?' የሚለው የመጀመሪያ ጥያቄው ነው፡፡

ሼኽ መሀመድ ለኢንቨስትመንት የተመቸ ሁኔታ ኖረም አልኖረም ሔጄ ሀብቴን እዚያ አፈስሳለሁ፡፡ ምክንያቱም አገሬን እወዳታለሁ!' ብለው ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ ሳይደረድሩ የመጡ ሀገር ወዳድ ናቸው፡፡



አሁን ባለ ሀብቱ ከቻይና፣ ከቱርክ፣ ከዚህም ከዚያም ብቅ ብቅ ማለት ለመጀመሩ አንዱ ምክንያት የእርሳቸው ፈር መቅደድ ይመስለኛል።

ሼኽ መሀመድ ሙዋዕለ ነዋያቸውን በአገራቸው በማፍሰሳቸው ብዙ መልካም ነገሮች ተፈጥረዋል። የውጭ ባለ ሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ በር ከፍቷል፤ ዋስትና ሰጪም ሆኗል። ምክንያቱም የውጭ ባለ ሀብት ለኢንቨስትመንት ከሀገር ሀገር ሲዘዋወር ኢንቨስት ሊያደርግ የፈለገበት ሀገር ውስጥ ስለኢንቨስትመንት ያጠናል፤ ሌሎች መኖራቸውንም ያረጋግጣል።

የሼኽ መሀመድ ኢንቨስትመንት ብዙ ኢትዮጵያውያንን የሥራ ዕድል ባለቤት አድርጓል። ኢንቨስትመንቶቹ ዘመናዊ አሠራርን ጭምር ይዘው ስለሚመጡ ተቀጥረው ለሚሠሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን የተግባር ትምህርት ቤቶች ኾነዋል።

አሁን በዚህ ሰዓት እንኳን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ባለሀብቶችና ኩባንያዎች እነማን ናቸው?’ የሚል ጥያቄ ሲነሳ በቅድሚያ ሼኽ መሀመድና ሚድሮክ ይጠራሉ። ለዚህ ዕውቅና ልንሰጥ ይገባል።

ሼኽ መሀመድ እንደ አንዳንድ የውጭ ባለ ሀብት ይህችን ሠራርቼና አዳብሬ፣ ኢንቨስትመንቴን አፈርጥሜና ገንዘብ ይገኔ እመለሳለሁ የሚል ዕቅድም ሃሳብም የላቸውም። ጭራሽ በውጭ ሠርተው ያገኙትን ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ዜጎች ዕድሉን ተጠቅመው እንዲያድጉና ሠልጥነው እንዲሠሩ አድርገዋል።

ሼኽ መሀመድ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከተሉትን የኢንቨስትመንት ፍልስፍና የታዘበ እኒኽ ሰው ለትርፍ የመጡ ወይስ ለሀገር ፍቅር? ብሎ መጠየቁ አይቀርም። ለእኔ ሁለተኛው ያመዝናል። በእኔ የሚመሩ የእርሳቸው ኩባንያዎች ሃያ አንድ ደርሰዋል። እነዚህ ኩባንያዎች የሚያገኙትን ትርፍ በአብዛኛው ለሠራተኛው ጥቅምና ለኩባንያዎቹ ዕድገት እንዲያውሉት መመሪያ ይሰጣሉ።

የትኛው ባለ ሀብት ነው ይኼን የሚያደርግ? እኒህ ሰው ባለ ሀብት ናቸው? ትርፍ እየሰበሰቡ ነው? ወይስ ከልባቸው አገራቸውን እያገዙ? ሼኽ መሀመድ ለአገራቸው ተነግረው የማያልቁ ነገር ግን በብዙ ሰዎች ዘንድ የማይታወቁ መልካም ተግባራትን አከናውነዋል። ለአገራቸው ሲሉ ያከናወኑት ነውና አንድ ቀን ታሪክ በገድልነቱ ይዘግበውና መልካምነታቸው በገሃድ ሲወደስ ይኖራል።

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** በአንድ ወቅት ጠዋት ከእንቅልፌ ስነሳ መንገዱን ጨርቅ አድርግልኝ ሳይሆን ታግዬ የማሸነፋቸውን ፈተናዎች አዘጋጅልኝ እላለሁ ብለው ነበር። ዛሬም ከዚህ ፍልስፍናዎ ጋር ነዎት?

**ዶ/ር አረጋ፡-** የሰው ልጅ እያንዳንዱ ቀን በከንቱ እንዲያልፍበት መፍቀድ የለበትም። ትናንት እንደገና አይመጣም። ዛሬ ቢሮ የተገኘሁት አዲስ ነገር ለመሥራት እንጂ ትናንት የሠራኋቸውን ነገሮች ለመደጋገም አይደለም። በየዕለቱ፣ በየሰዓቱና በየደቂቃው አዳዲስ ነገሮች መፈጠር አለባቸው። አዳዲስ ነገሮች የሚፈጠሩት ደግሞ ከችግር ውስጥ ነው።

የሚያስቸግር ሠራተኛ ቢኖር እሰየሁ ነው። እንድትሻሻል ያደርግኻል። ባገኘኸው ቁጥር ጸጥ፤ ስትሄድም ጸጥ፤... ዛሬም፣ ነገም፣ ከነገ ወዲያም ጸጥ ከሆነ አንተም እርሱም አትሻሻሉም። ስለዚህ ከሠራተኛው መካከል የተወሰነው በጥፍርህ ሊያቆምህ አቅም ያለው መሆን አለበት። ተገዳዳሪ ሃሳብ የሚያቀርብ፤ ስትናገርም ስትሠራም አማራጭ የሚያቀርብ ሰው መኖር አለበት። ከቤቴ ወደዚህ ስመጣ በሃሳብ የሚገዳደረኝ ሰው እንዲኖር እፈልጋለሁ።

ጠዋት እንደ መጣሁ ለግማሽ ሰዓት ያኽል መንገድ ዳር ላይ ካለው ሜዳ መኪናዬን አቁሜ እቆያለሁ። አንዳንዱ ሠራተኛ መጥቶ የግሉን ችግር ያቀርብልኛል። እንደ አለቃ ችግሩን ብትፈታለት ቀንህ ብሩህ ሆኖ ይውላል። ዝም ብለህ ቢሮ ገብተህ ወረቀት ብታገላብጥ ምኑ ደስ ይላል? እረኛ ነኝ ብለህ የምታስብ ከኾነ እረኛ እንድትሆን ያበቁህን ሠራተኞች እንዲያዩህ ማድረግ አለብህ።

እየተደበቅህ እረኛ መሆን አትችልም። ራስህን ለሰዎች ቅርብ ማድረግ አለብህ። በመሪነት ሥራዬ ተግዳሮት (challenge) አልፈራም፤ ይልቁኑ ችግሩን ተጋፍጬ የማቸንፍበትን ጥበብ ፈጣሪ እንዲሰጠኝ እጸልያለሁ። አንዳንዱ ችግር ደስ ይላል። ልትወጡት የማትችሉት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከዘረጋችሁት የአፈታት ሥርዓትና ከቡድናችሁ ጋር በትጋት ከሠራችሁ በመጨረሻም በድል ትወጡታላችሁ።

**የፒራሚዱ ጫፍ፡-** በመጨረሻ ለአንባቢዎቻችን የሚያስተላልፉት መልዕክት አለዎት?

**ዶ/ር አረጋ፡-** ዕድሜ ሰጥቶኝ የዛሬ ሠላሳ ዓመት ኢትዮጵያን የማየት ዕድል ቢገጥመኝ አሁን ካለችው ኢትዮጵያ ፍጹም የተለየች ሀገር እንደምትኾን አምናለሁ።

ሀገራችን የምትታየኝ ከፊት ከፊት እየቀደመች አገሮችን ስትመራ ነው። ይኼን ለማለት የሚያስደፍረኝ ለዕድገቷ አስፈላጊ የሆኑትን ግብዓቶች በሙሉ የታደለች መሆኗ ነው። ባሕሏ፣የአየር ንብረቷ፣ የተፈጥሮ ሀብቷ... ወዘተ ማን ተወዳድሯት? የሌለን ነገር ቢኖር የዘመኑ ዕውቀት’ና ካፒታል ብቻ ነው። ይኼም ቢኾን ይመጣል ብዬ አምናለሁ። የአገራችን ዕድገት በሙሉ ልብ ሊደገፍ የሚገባው ነው።

የሥራ ባሕላችን እየተለወጠ ስለመሆኑ አበረታች ነገር እያየን ነው። ጠዋት ከእንቅልፉ ተነስቶ “ቁርሴን አክስቴ ቤት እበላለሁ።...ገንዘብ ከአጎቴ እወስዳለሁ...” በሚል ወጣት ፈንታ “...ካልሠራሁ በስተቀር ገንዘብ አላገኝም። መብላትም መኖርም አልችልም” የሚለው ወጣት እየበረከተ ነው። በምዕራቡም ዓለም ጠዋት ሲነጋ ሰው የሚታየው ሥራው ነው።

ድሮ ጠዋት ከመኝታ ስንነሳ “...ግዴለም ምን አስቸኮለኝ? ከሰዓት በኋላም ቢሆን እሠራዋለሁ” ማለት በእጅጉ የተለመደ ነበር። አሁን ግን “ካልተሠራ ምንም ነገር አይቻልም” በሚል ሥነ-ልቦና የተቃኘ እንቅስቃሴ እያየን ነው። ይኼ መጠናከር አለበት። ሥራ ባሕል (Culture) እየሆነ መሄዱ እየታየ ነው።

የዕድገት አቅጣጫችን ሙከራ የሞላበት ቢኾንም ውጤት እያየንበት ነው። ይኼን ሙከራ በተግባር እየመነዘሩና እሴት እየጨመሩ መኼድ እንጂ አቅጣጫን ያለአግባብ መለወጥ ጥቅም የለውም። በተያዘው አቅጣጫ ላይ ገንቢ ግብዓቶችን እያከሉ፣ እያሻሻሉና እያከሉ ወደ ፊት መጓዝ ነው። ይህን ማድረህ ለእናት ሀገር ያንሳታል።

**የፒራሚዱ ጫፍ፡** እናመሰግናለን።

**ዶ/ር አረጋ፡** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

***Address:***
***MIDROC Technology Group***
***Office of the Chief Executive Officer,***
***Tel: +251-011-371-8900***
***Fax: +251-011-371-5988 / 372-4977***
***P.O. Box: 5787, Addis Ababa Ethiopia***
***E-mail: contact@midroc-ceo.com***
***Website: www.midroc-ethiotechgroup.com***

*በነፃ የሚታደል (Distributed at no Cost)*